የምሳለ ጸሎት

ቅድመ ዓለም የነበርክ ዓለምን አሳልፈህ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮትህ ለዘለዓለም ጸንተህ የምትኖር አብ ሆይ፥ አቤቱ ማረን (ሃሌ ሉያ)። ቅድመ አለም የነበርክ ዓለምን አሳልፈህ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመንግሥትህ ለዘለዓለም ጸንተህ የምትኖር ወልድ ሆይአቤቱ ይቅር በለን (ሃሌ ሉያ)። ቅድመ አለም የነበርክዓ ምን አሳልፈህ ከአብ ከወልድ ጋር ለዘለዓለም በሥልጣንህ ጸንተህ የምትኖር መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አቤቱ በቸርነትህ አስበን (ሃሌ ሉያ)። ላንተ ፍጹም ምስጋናን እናቀርባለን፣ እናሳርጋለን። መሐሪ ቸር ሆይ፣ ኃጢአታችንን አስተሥርይልን። አቤቱ አድነን። የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ሆይ፣ ነፍሳችንንና ሥጋችንን ላንተ አደራ እናስጠብቃለን። አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ይቅር በለን። አቤቱ በቸርነትህ ብዛት ኃጢአታችንን ደምስሰህ አጥፋልን፤ ይቅርታህንም ላክልን። ቸርነት ይቅርታ ካንተ ዘንድ ነውና ሃሌ ሉያ። መሐሪና ይቅር ባይ የምትሆን አብ ሆይ፣ ማረን። መሐሪ ቸር አባት ሆይ፣ ይቅርታህን ላክልን እንጂ የቀድሞ በደላችንን አስበህ አታጥፋን። በቸርነትህ ላይ አንተ መሐሪ ነህና። ለሚጠሩህ ሁሉ ቸርነትህ ብዙ ነው። በእውነት የሚጠሩህን ሁልጊዜ ትሰማቸዋለህ። የማዳን ችሎታ አለህ። በእውነትም የማዳን ችሎታ ያለህ አንተ ብቻ ነህ። አምላካችን ሆይ፣ ቃልህ እውነት ነውና ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ አብን እንለምነው። እሱ አብ የለመኑትን አይነሳምና። ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለሱ ክብር ምስጋና ይገባል። ቅድመ ዓለም ለነበረ ዓለምን አሳልፎ ለሚኖር ለሁሉ ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይገባል።

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ አሁንስ ማነው ተስፋዬ? እሱ እግዚአብሔር አይደለምን? አቤቱ ነፍሴን በእጅህ አደራ አሰጣለሁ። ወደ ምሕረት አምላክ ነፍሴን አማጽናለሁ። ወደ ክብር ንጉሥ ነፍሴን አደራ አሰጣለሁ። በጌታዬና በአምላኬ ነፍሴን አማጽናለሁ። አቤቱ ከክፋ ነገር ሁሉ ነፍሴን አድናት። ኑ እንለምነው፤ አሁንም እንለምነው፤ እንማልደው። እውነተኛው አምላካችን ቃሉ አይታበልምና ሁሉንም ማድረግ ይችላል። የሚሳነው ነገር የለም። የነዳያን አምላካቸውና ተስፋ ለቆረጡ የታመነ ተስፋቸው ነው። አቤቱ ወዳንተ እንማጸናለን። ሁለተኛ ጊዜ አቤቱ ወዳንተ እንማልዳለን። ሦስተኛ ጊዜ አቤቱ ወዳንተ እንጠራለን። አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝክ እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን።

አቤቱ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ይቅር በለን። አቤቱ መንፈሰ ጽድቅ ጸራቅሊጦስ ሆይ፣ ኃጢአታችንን አስተሥርይልን። ለዘለዓለሙ ከኛ አትለይ። አቤቱ በችግራችንና በመከራችን ጊዜ ረዳት ስለሌለን ከአንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለም። አቤቱ በመስቀል ላይ ሳለህ ኤሎሄ ኤሎሄ (አባት ሆይ) በማለት በተጣራኀው አጠራርህ ምህላችንን (ጸሎታችንን) ትሰማን ዘንድ እንማጸናለን። አቤቱ አምላካችን ሆይ፣ ከሠርክ እስከ ነግህ እንደጠበቅከን እንዲሁ ከነግህ እስከ ሠርክ ጠብቀን። አቤቱ አምላካችን ሆይ፣ ሌሊቱን ሁሉ እንደጠበቅከን ቀኑንም ሁሉ እንዲሁ ጠብቀን። አቤቱ መድኃኒታችን ሆይ፣ ሰዓተ መዓልቱን ባርከህ ቀድሰህ በሰላም አሳድረን። እመቤታችን ማርያም ሆይ፣ የልጅሽ የእጆቹ ሥራዎች የምንሆን እኛ በከንቱ እንዳንጠፋ በየዕለቱና በየሰዓቱ ለምኝልን አቤቱ ቀኑን ሁሉ ሌሊቱንም ሁሉ የሠራነውን ኃጢአታችንን ይቅር ትልልን ዘንድ ስለ እናትህ ማርያም እንማጸንሃለን። አቤቱ ታድነን ዘንድ ቅዱስ ፈቃድህ ይሁንልን። አቤቱ ዝም አትበለን። ቸልም አትበለን። አቤቱ እኛ ፈራሽ በስባሽ መሆናችንን አስበህ ጠብቀን።

አቤቱ ቅድመ ዓለም የነበርክ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር ምድርህን (ኢትዮጵያን) ይቅር በላት። ክብርህን ሞገስህን ስጣት። ሰላምን አውርድላት። አቤቱ ልመናችንንና ጸሎታችንን ስማ። ኃጢአታችንንም አስተሰርይልን። አቤቱ የዕዝራን ጸሎትና ልመና እንደሰማኸው ጸሎታችንንና ልመናችንን ተቀበል። ምሳላችንን ስማ። ሰላምህን ስጠን። ለሁልጊዜም ከመካከላችን አትራቅ አሜን።